# የጥላቻ ብዕር እውነት አይናገር...

**(ይገረም አለሙ)**

**August 19, 2015 -**

ጸሀፊው ወርቁ አሰፋ (ዶ/ር) የጽሁፉ ርዕስ ተናግረው የሚያናግሩ ሰዎች ምክንያተ ጽሁፍ ታሪኩ አባዳማ የተባሉ ጸሀፊ በጸሀፊ ደምስ በለጠ ጽሁፍ ላይ የሰጡት አስተያየት የገጽ ብዛት ስምንት፡፡ (የታሪኩ አባዳማ ጽሁፍ 2 ገጽ ነው)

ጸሀፊ ደምስ በለጠ መልስ ቢሰጡበት ተመራጭም ተገቢም በነበረው ጉዳይ ላይ ወርቁ አሰፋ(ዶ/ር) ምላሽ መስጠታቸው ጥሩም ባይሆን መጥፎ አይደለም፡፡ ነገር ግን እውነቱን ለማጥራት ብለው ጀምረው እውነት ያልሆኑ ነገሮችን ፤ ነገርና የወለዱት ልጅ ሲመስል ጥሩ ነው ብለው የማይመስል ነገር፤ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ብለው ያልዋሉበትንና የማያውቁትን፣ አባዳማን በንዴት ጻፍክ ብለው እየወቀሱ ርሳቸው እርር ድብን ብለው ብእር ማንሳታቸውን የነገርንን ጽሁፍ አስነበቡን፡፡

ጽሁፉ እንደብዛቱ ብሎም በንዴት የቀለመ በጥላቻ የተበከለ እንደመሆኑ ብዙ ሊባልበት የሚችል ቢሆንም ወደዛ አልገባም፡፡ የእኔ ትኩረት የሚሆነው በስማ በለው ሳይሆን በአካል የማውቀውና በተግባር ያለፍኩበት ጉዳይ በጸሀፊው ባልነበረ መልኩ ተገልጹዋልና ለአንባቢያን የአይን ምስክርነት መስጠት ላይ ነው፡፡ የሚያውቁት ነገር ሲዋሽ ዝም ማለት አንድም ተባባሪ መሆን ነው፤ ሁለትም የህሊና ዕዳ ነው፡፡

በቅድሚያ የምስማማበትን ሀሳብ ልግለጽና ጥያቄ ላንሳ፣ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ከሻዕቢያ ጋር በሚደረግ ቁርኝት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚመጣ በጎ ነገር መኖር አለመኖሩን በመረጃ በተደገፈ ተጨባጭ ጉዳይ ላይ ተወያይቶና ተነጋግሮ መፍትሄ በመፈለግ ነገሩን መቋጨት ሲገባ፤ በሚለው ሀሳብ እስማማለሁ፡፡ ጥያቄ ግን አለኝ ከሻዕቢያ ጋር ግንኙነት ከተጀመረ አመታት ተቆጥረዋል ታዲያ ጉዳዩ ለምን ቀደም ብሎ አልተነሳም? ለምን ይህ ወቅት ተመረጠ? ዛሬ የተግባር እንቅስቃሴ ሲጀመር መጻፉና መነገሩ ምን ለማስገኘት ወይንም ለማግኘት ነው? በጽሞና መነጋገር እንዲህ ከመጠየቅና ከመመለስ ይጀምራል።

አንድ ግላዊ ጥያቄ ላክል፣ ፍርድ ቤት ለምስክርነት የቀረበ ሰው መናገር ከመጀመሩ በፊት ችሎቱ ከተከሳሽ ጋር ጸብ ወይንም ዝምድና አለህ በማለት ይጠይቃል፡፡ ይህን እንዳነሳ ያደረገኝ በጽሁፎ ውስጥ ስለ ፕ/ር ብርሀኑ የገለጹት ነው፤ የግል ጸብ አላችሁ? ወይስ ከአርበኞች ግንባር ጋር የሚያገናኝዎት ጉዳይ አለ? በዶ/ር ብርሀኑ ምክንያት ያጡት ነገርስ አለ? ወደ ዋናው ጉዳይ ላምራ፡፡

**1 –** በዚያው አንፃር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሥርዓቱ የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ ለቋቋሙና በ **1997** ዓ/ም (እ.አ.አ **2005** ዓ/ም) በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ተሳትፈው ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ሥርዓት ለመመስረት ባደረጉት ዝግጅት፤ በውጭና አገር ውስጥ ባለ ሕዝብ ግፊትና ጫና በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ሕብረት ፈጥረው እንደነበር ይታወሳል። በተፈጠረው ሕብረት ውስጥ በነበሩ ድርጅቶች መሃከል በተነሳው መጠነኛ አለመግባባት፤ አንጋፋው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና ኢዴፓ ከሕብረቱ እራሳቸውን አግልለው ሌላ አቀናጅቶ ለውጤት የሚያበቃ የጋራ ድርጅትን መሠረት ሲጥሉ፤ ከሕብረቱ ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ ለማበር ቀና ነበሩ። (የራሳቸውን ጽሁፍ ነው ኮፒ ያደረኩት)

ይህ አገላለጽ ከፊል እውነት ከፊል ሀሰት ነው፡፡ በዝርዝር ለማቅረብ ብዙ ገጽ ይፈጃል አንባቢንም ያሰለቻል፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ራሱን ችሎ እመለስበታለሁ፡፡ እውነቱ በአሜሪካን ሀገር በተካሄደ ጉባኤ መኢአድና ኢዴፓ ተሳታፊ ሆነው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃህ) አባል መሆናቸው ነው፡፡ ቀሪው ገለጻ ማሳመሪያ ወይም ማድመቂያ ነው፡፡

አንደ አንጋፋነቱ አንድም የሀላፊነት ቦታ ያልደረሰው መኢአድ ከህብረቱ እንደሚወጣ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የጻፈው ለጉባኤ የላካቸው ተወካዮቹ ገና ወደ ሀገር ቤት ሳይመለሱ ነው፡፡ ካቀረባቸው ምክንያቶች ውስጥ የጉባኤው ሰነዶች ይሰጡኝ፣ በስምምነቱ መሰረት የህብረቱ ዋና ጽ/ቤት ሀገር ውስጥ ይሁን፣ ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል፤ ለጥያቄው ምላሽ ባለማግኘቱ አንድም ተሳትፎ ሳያደርግ ነው ከህብረቱ የወጣው፡፡

ኢዴፓ ከመጀመሪያው ለጉባኤ ወደ አሜሪካ ያቀናው ተባብሮ መስራት አይፈልግም በሚል የጉባኤው አዘጋጆች የሚያወርዱበትን ዘመቻ በመፍራት እንጂ በነገሩ አምኖበት እንዳልነበረ የወቅቱ አመራሮች ቢበታተኑም በህይወት አሉና ጠይቆ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲህም ሆኖ የዋና ጸኃፊነት ቦታ ደርሶት እንደምንም እስከ ሁለተኛው ጉባኤ ደርሶ ስምምነታችን አልተከበረም፣ ህብረቱ በውጪ ባሉ ኃይሎች ተጠልፏል ወዘተ በማለት ከህብረቱ ወጣ፡፡ እናም ሁለቱም ፓርቲዎች ያነሱት ጥያቄ መጠነኛ አለመግባባትን ሳይሆን መሰረታዊ ልዩነትን ነው የሚያሳየው፡፡

መኢአድና ኢዴፓ ከህብረቱ ራሳቸውን አገግልለው ሌላ አቀናጅቶ ለውጤት የሚያበቃ የጋራ ድርጅትን መሰረት ሲጥሉ፤ ተብሎ የተገለጸውም እውነታው እንዲህ አይደለም፤ የሁለቱ ድርጅቶች ተወካዮች አሜሪካ ለጉባኤ እንደሄዱ በዛ ያገኙዋቸው የሁለቱም ደጋፊ ኢትዮጵያውያን፤ የፕሮግራም ልዩነት ሳይኖራችሁ ሁለት መሆናችሁ ምንድን ነው ብለው ጠይቀው፤ ከዚህ በኋላ አንድ ካልሆናችሁ ሁለታችሁንም አንረዳም ብለው አስገድደው አደራደሩዋቸው፡፡ በዛ መነሻነትም አገር ቤት የጋራ የውህደት አመቻች ኮሚቴ አቋቁመው ብዙ ከተሰራ በኋላ መጀመሪያም በእምነት ሳይሆን በማስገደድ የተጀመረ ነበርና በስልጣን ክፍፍል ባለመስማማት ሳይሳካ ቀረ፡፡ ይህ ሲሆን ኢዴፓ የህብረቱ አባል እንደነበረ ነው፡፡ ከህብረቱ ጋር በጋራ ለማበር ቀና ነበሩ የተባለው በፍጹም አይደለም፡፡ መጀመሪያ ነገር ኢዴፓ ከመኢአድ በወጡ ወጣቶች የተመሰረተ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሁለቱ በጋራ የሚያብሩ አልነበሩም፡፡ በተናጠልም ቢሆን ሁለቱም ከኢዴኃህ ጋር ፍቅር አልነበራቸውም፡፡ እንኳን እነሱ የሀገር ቤቱን አመራር እየተፈራረቁ ይዘውት የነበረው ፕ/ር በየነና ፕ/ር መረራ አንኳን አንዴት እንደተለያዩ የሚታወቅ ይመስለኛል፡፡ አንድ ዕጩ ያላወዳደሩ ሰዎች አሜሪካ ተቀምጠው ሰለምርጫ **97** ለመወሰን ሲቃጣቸው ነው ሁለቱ የተለያዩት፡፡

**2 –** ከሻዕቢያ ጋር የባድሜን ጦርነት ተከትሎ ሕወአት ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈል፤ ለወያኔ/ኢህአዲግ ቀረቤታ ያላቸው ምሁራን በታማኝ ተቃዋሚነት ፓርቲ መሥርተው ሕዝባዊውን ትግል እንዲቀላቀሉ ተደርጓል። ዶ/ር ብርሃኑና ፕሮፌሰር መስፍን የመሠረቱት **"**ቀስተ ደመና**"** እና የፕሮፌሰር አለማየሁ ረዳ **"**ኢዲሊ**"** መኢአድና ኢደፓን በመጠጋት **"**የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ**"** አባል ሆኑ፡፡

በጣም የሚገርም ድፍረት ነው፡፡ አንባቢን መናቅም ነው፡፡ በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ይታዘቡኛል አውነቱንም ሊናገሩ ይችላሉ ተብሎ አንዴት አይታሰብም፡፡ ለነገሩ የጥላቻ ግርዶሽ ሁሉን ነገር ነው የሚከልል፡፡

የሻዕቢያ እና ወያኔ ጦርነት **1991** ዓም **(**እ**.**ኢ**.**አ**)** ነው የተካሄደው፤ እነ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ቀስተ ደመናን መስርተው ህጋዊ ምስክር ወረቀት ያገኙት በህዳር ወይንም በታኅሣሥ **1997** ዓም ነው፡፡ ታዲያ እንዴት ነው ጸሀፊው ያዛመዱት፤ ታማኝ የተባሉትስ የትኞቹ ናቸው፤ ወያኔ በግፍ አስሮ በሀገር ክህደትና በዘር ማጥፋት ወንጀል ከሶ እድሜ ልክ የፈረደባቸው ታማኝ በመሆናቸው ነው**?** አረ እየተስተዋለ፡ ጥላቻም ልክ አለው፤ ውሸትም ገደብ፡፡

ሌላው አጀኢብ የሚያሰኘው የቅንጅት መስራቾችን ጠጋ ብለው አባል ሆኑ የሚለው ነው፡፡ ጉድ ነው መቼም፡፡ ሂደቱን በቅርብ ስለማውቀው ለአንባቢያን ትንሽ ላብራራው፡፡

በ **1992** ዓም በኢተፖድህ ድጋፍና በዶ/ር መረራ ፓርቲ **(**ኦብኮ**)** አስተባባሪነት በሀገር ቤት የሚገኙ ስድስት ፓርቲዎች የትብብር መድረክ መሰረቱ፡፡ ዶ/ር በየነ አልነበሩበትም፡፡ የ **1993** ቱ የወረዳና ቀበሌ ምርጫ ሲያበቃ የትብብሩም ግዜ አበቃና የፓርቲዎቹ መሪዎች ግለ ግንኙነት ሲያደርጉ ቆይተው መኢአድ ኢዴፓ ኦብኮና ፕ/ር በየነ በአማራጭ ኃይሎች ስም አባል የሆኑበት ግንኑነት ተጀመረ፤ ብዙም ሳይቆይ ኢዴፓን አስወጡና ሶስቱ ትብብር ለዴሞክራሲ በኢትዮጵያ **(**ትዴኢ**)** የተባለ መሰረቱ፡፡ የአሜሪካው አዴኃህ ሲመሰረት የውኃ ሽታ ሆነ፡፡ ከላይ የተገለጸው የመኢአድና የኢዴፓ ውህደትም በጉጉት ሲጠበቅ አንዳይሆኑ ሆነና ርስ በርስ መወነጃጀል ውስጥ ገቡ፡፡

በምርጫ **92** ውጤት ላይ የተሰራ ጥናት ያረጋገጠው በተለይ አዲስ አበባ ላይ ተቀዋሚዎች በድምር ውጤት አሸንፈው መሸነፋቸው በምርጫ **97** ትም ሊደገም መሆኑ ያሳሰባቸው ተዋቂ ምሁራን ፓርቲዎችን መሸምገል ጀመሩ፤ ግለሰባዊ በሆኑ ተልካሻ ምክንያቶች ግዜ የፈጀው ሽምግልና አንበለው ድርድር አንዳችም መልክ ሳይይዝ ምርጫ **97** እየተቃረበ በተለይ ኢዴፓና መኢአድ ፉክክራቸው እየጠነከረ ሄደ፡፡ በዚህ ግዜ ምሁራኑ ጠረጴዛ ላይ ያረፈው አማራጭ ተበታትነን ሁለቱ ፓርቲዎች ውስጥ አንግባና ወደ አንድነት አናምጣቸው ወይም አላማው ፓርቲዎችን ማቀራረብ ብቻ የሆነ አንድ ፓርቲ አንመስርትና ማእከል ሆነን ለውህደት እንስራ የሚል እንደነበረና ሁለተኛው የተሸለ ውጤታማ አንደሚሆን ስምምነት ላይ ተደርሶ ቀስተ ደመና እንደተመሰረተ በወቅቱ በተለያየ መንገድ ተገልጸ**垸**ል፡፡ ምርጫ **97** እየተቃረበ ስለነበር ቀስተ ደመናን የመመስረትና ለቅንጅት መሰረት የመጣል ስራዎች ጎን ለጎን ነው የተሰሩት፡ በዚህ ሄደት የወጣውን መመዘኛ ያሟሉ አራት ፓርቲዎች የአጭር ግዜ ግቡ ምርጫ በጋራ መወዳደር የረዥም ግቡ ደግሞ በውህደት አንድ መሆን የነበረውን ቅንጅትን መሰረቱ፡፡ በምርጫ **97** ትም ታሪክ ሰሩ፡፡

**3-** ዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅት ውስጥ አንጃ እንዲፈጠርና ድርጅቱ እንዲከፈል በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ሰው ነበሩ። አቤት እግዚኦ**!!** በሞቴ ዶ/ር ያኔ የት ነበሩ፡፡ እኔ የማውቀው የመኢአድና ኢዴፓ ቅራኔ ቅንጅትን ሲያናውጠው እየሸመገሉ መልክ ያሲያዙ፤ ቅንጅት ከአንዴም ሁለትና ሶስት ግዜ የገጠመውን የመፍረስ አደጋ አልፎ ለምርጫ እንዲቀርብ ትልቁን ድርሻ የተወጡ መሆናቸውን ነው፡፡ በወቅቱ ሂደቱን በቅርብ እከታተል ነበርና ጥቂት ማስረጃ ላቅርብ፡፡ በቅንጅት የቀረበውን አብዛኛውን ዕጩ ያቀረቡት መኢአድና ኢዴፓ በእጩ ምደባ ላይ ሳይሰማሙ ቀርተው ቅንጅት አደጋ ላይ በወደቀበት ግዜ ሁለቱን የመገላገል ኃላፊነት ወስደው ቀን አመራሮቹን በተናጠል አነጋግረው አዳራቸውን የሁለቱም ፓርቲ ተወካዮችን በቅንጅት ቢሮ ይዘው ያልተስማሙባቸውን ቦታዎች ዕጩዎችን በማደላደል ቅንጅትን ከአደጋ ታድገውታል፡፡

አንድ ላክል፤ በዕጩዎች ማስመዝገቢያ የመጨረሻ ቀን መኢአድ ለብቻው ምልክት መርጦ የራሱን ዕጩዎች በመኢአድ ስም አስመዘገበ፡፡ ይህ ደግሞ ለቅንጅትም ሆነ ለመኢአድ ትልቅ አደጋ ነበር፡፡ ለቅንጅት የመወዳደር አቅሙ በእጩዎቹ ማስ ይዳከማል፡፡ ኢ/ር ኃይሉም አለማስተዋላቸው ነው አንጂ በዛን ወቅት ከቅንጅት ተነጥሎ ወጥቶ መኢአድን ማንም አይመርጠውም ነበር፡፡ ይህ እንደተሰማ ትልቁን ማዳን

ስራ የሰሩት የቀስተ ደመና ሰዎች በተለይ ደግሞ ፐ/ር ብርሀኑ ነጋ ነበሩ፡፡ ቀን ስምንት ሰዓት የተሰበሰቡ ኢ/ር ኃይሉ በመኢአድ ሊቀመንበርነታቸው የመሻሪያ ደብዳቤ፤ በቅንጅት ሊቀመንበርነታቸው የቅንጅትን እጩዎችን የማሳወቂያ ደብዳቤ እንዲጽፉ ተደርጎ ለሌት ዘጠኝ ወይንም አስር ሰአት ስብሰባው ማለቁን አውቃለሁ፡፡

4 – ይህም ድርጅት ወደ "መኢአድ"ና "አንድነት" ሲከፈል ከአንድነት ጋር ጥቂት ተጉዘው ባለመስማማታቸው፤ እራሳቸው የሚመሩት ግምቦት 7 የተባለ ድርጅት መሰረቱ። ሌላው ቢቀር ፊትና ኋላን መለየት አንዴት ይቸግራል? አንባቢስ ይህን አይገነዘብም ተብሎ አንዴት ይገመታል? የቅንጅት አመራሮች ሀምሌ 13/1999 ዓ.ም ከቃሊቲ ወጥተው አውሮፓና አሜሪካ የሄዱት በጳጉሜ ነው፡፡ ፐ/ር ብርሀኑ ከዛ በኋላ ወደ ሀገር ቤት አልተመለሱም፡፡ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የተመሰረተው ደግሞ ሰኔ 11/2000 ዓ.ም ነው፡፡ መለስ ብሎ በወቅቱ የተጻፉትን በማንበብ ይህን በቀላሉ ማወቅ የሚቻል ሆኖ እንዴት ሆኖ ነው ፐ/ር ብርሀኑ ነጋ ከአንድነት ጋር ቆይተው ባለመስማማታቸው ግንቦት ሰባትን መሰረቱ የሚባለው፡፡ የሀገሬ ሰው ትንሽ ቆሎ ይዞ ወደ አሻሮ ጠጋ እንደሚለው ሲዋሽም ትንሽ እውነት ይዞ ቢሆን ባያምርም ትንሽ መልክ ይኖረዋል፡፡

5 – ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ሊያቀራርቧቸው ካሰቡት ነፃ አውጪ ታጋዮች እጅግ በጣም የሚያራርቃቸው አንድ ወሳኝ ቁምነገር ቢኖር በዓላማቸው ፀንተው በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ለመርጋት የሚያስችል ባህርይና የመንፈስ ፅናት ማጣታቸው ነው።

ጸኃፊው ይህን ሲሉ ሌላው ቢቀር ራሳቸው የነገሩንን አላስተዋሉም፡፡ ኢህአፓ እንደነበሩ ከዛም ከሁለት አስርት አመታት በኋላ ቀስተ ደመና (ቀስተ ደመናና ቅንጅት በአንድ ነው የሚታዩት) አሁን ደግሞ ግንቦት 7፤ ይህን ነው ጽሁፉ ውስጥ ያገኘነው የፐ/ር ብርሁኑ ነጋ የፓርቲ ሽግግር፡፡ እያንዳንዱ የራሱ ምክንያት አለውና ከየትኛው ነው በዓላማ ጽናት ጉድለት፤ በመንፈስ ጥንካሬ እጦት፣ በመልካም ባህርይ ማነስ የተለዩት? መቼም ከኢህአፓ አይሉም፡፡ ከቀስተ ደመና እንዳይሉ በቅንጅት ውህደት ፈርሷል፡፡ ከቅንጅት እንዳይሉ ደግሞ እነርሱ ታስረው ቅንጅት ለአቶ አየለ ጫሚሶ መሰጠቱን አለም የሚያውቀው ነው፣ እንኳን አበሻው ፈረንጁም፤ ከአንድነት እንዳይሉ ከላይ በማስረጃ እንዳሳየሁት አንድነትና ፐ/ር ብርሀኑ ነጋ አይተዋወቁም እህሳ ምን ይላሉ ወገኔ ያገሬ ልጅ፡፡

አበቃሁ ፍቅር ይስጠን ጌታ።